"ተመስገን በዕልልታ"

ሰው በላው የወያኔ ትግሬ ወንጀለኞች ሁሉ በህግ ሊጠየቁ በመረጃ እስር ቤት ገቡ ማለትን ሰምቶ ተመስገን አምላኬ የማይል ኢትዮጵታዊ የሚኖር አይመስለኝም። የንፁህን ደም ይጮህልና ፈጣሪ አምላክ ጊዜው ሲደርስ መልስ ሰጠ ማለት ይቻላል። በርግጥ የወንጀሉ ተባባሪዎች፣ ተጠቃሚዎች፣ በጎሳ ፓለቲካ የተጨማለቁና ትግሬ ከሌላው ሁሉ የበለጠና የተሻለ ነው ብለው ያመኑ የዋህ ፍጡሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይገመታል። እኔ ግን የነዶ/ር አብይ የለውጥ ሀይል በነዚህ ጅቦች ቀድሞ እንዳይበላ ስጋት ነበረኝና ዛሬ የዶ/ር አብይ አስተዳደር "ጥርስ እያወጣ" መሆኑን ተገንዝቤ ስጋቴ ቀንሶልኛል። አሁንም በነፃ የሚንቀሳቀሱ ብዙ ወንጀለኞች ስላሉ ሁሉንም ሰብስባችሁ አስገቡ። ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎናችሁ ነው እላለሁ።

አገርና ወገን - ማገልገል ቀረና
በትግሬ ወያኔ - ጉድ ታየ ገመና
ስልጣንን ለዝርፊያ - ደግሞም ለግድያ
ለግል ጥቅማጥቅም - ትውልድ ማሰቃያ
ከሌላው ለመብለጥ - አገር በዕዳ አስይዞ
ሲዘርፍ የኖረው - ሰው በላ ተይዞ
በደም የጨቀየው - ወያኔ ተይዞ
ፍትህ ለሰፊው ህዝብ - ህወሀት ተከዞ
ማየት ተስፋችን ነው - ለቀጣዩ ጉዞ።
ኢትዮጵያ አምላክ አላት - ሁሌም አናመንታ
ተያይዘው ገቡ - ሰማነው በደስታ
ለዚህ ቀን ላበቃን - ለላይኛው ጌታ
ደስታችን ይሰማ - ተመስገን በዕልልታ።

ከዘውዲቱ የማነ
2018-11-12